# የ“ቻይ” ዓለም አቀፍ የአሰራር እና የሥነ-ምግባር ደንብ

## **ቅጥያ 3፡** የወሲብ ብዝበዛን፣ በደል እና ትንኮሳን የመከላከል ፖሊሲ (PSEAH)

ክሊንተን ሄልዝ አክሰስ ኢኒሺዬቲቭ (ቻይ) የወሲብ ብዝበዛን፣ የወሲብ በደልን ወይም የወሲብ ትንኮሳን አይታገስም። ቻይ በተባበሩት መንግስታት ዋና ፀሀፊ በልዩ እርምጃዎች ቡሊቲን እ.ኤ.አ. በ2003 የተመሰረተውን የወሲብ ብዝበዛን እና በደልን መከላከልን አስመልክቶ የተቀመጡትን ዋና ዋና መርሆዎችን አጥብቆ በመደገፍ ዓለም አቀፍ ለትርፍ ያልተቋቋመ ማህበረሰብን ይቀላቀላል። ሁሉም ሰው ከወሲባዊ ጥቃቶች ነፃ ሆኖ  የመኖር መብት እንዳለው እናምናለን።

ይህ ፖሊሲ በማንኛውም ጊዜ ከተጠቃሚዎችና ከሕዝብ ጋር ያላቸውን ግንኙነት በተመለከተ፣ በሁሉም የቻይቻይ ሰራተኞች ላይ፣ በሁሉም ጊዜያት ተፈጻሚ ይሆናል። (የቻይ ዓለም ዓቀፍ የአሰራር እና የሥነ-ምግባር ደንብ በቻይ ሰራተኞች ወይም በተባባሪ ድርጅቶች ወይም ከቻይ ጋር በሚተባበሩ የመንግስት ኤጀንሲዎች ሰራተኞች ላይ የሚፈጸምን ያልተገቡ ወሲባዊ ባህሪያት ይሸፍናል። እባክዎን አክብሮት የተሞላበት የሥራ ቦታ መፍጠር እና መጠበቅ የሚለውን ክፍል ይመልከቱ።)

ሁሉም የቻይ ሠራተኞች የሚከተሉትን ማድረግ አለባቸው፡

- ሥነ-ምግባር የተሞላበት ባህሪ ማሳየት፣ ሁሉንም ግለሰቦች በክብር እና በአክብሮት መያዝ እና ከማንኛውም የወሲብ ብዝበዛ፣ በደል ወይም ትንኮሳ ድርጊት  ከመሳተፍ መቆጠብ።
- ሁሉም ሰራተኞች እና ተጠቃሚዎች ተቀባይነት የሌላቸው ባህሪዎችን ለመለየት እና ስለመብቶቻቸው እና ስጋታቸው ለመወያየት በሚችሉበት አካባቢ ላይ እገዛ ማድረግ። አስተዳዳሪዎች ይህንን አካባቢ ለማስጠበቅ የተለየ ሀላፊነት አለባቸው።
- ማንኛውም   የወሲብ ብዝበዛ፣ በደል ወይም ትንኮሳ የጥርጣሬ  ጉዳዮችን አስመልክቶ፣ አግባብነት ባለውአሰራሮች መሰረት ስጋቶችን ወዲያውኑ ማንሳት።
- ለሚመለከታቸው ሁሉ የግል ጉዳዮች በተለይም ለተጎጂዎች መብት እና ደኅንነት ልዩ ትኩረት በመስጠት በማንኛውንም የቻይ ምርመራ ሙሉ በሙሉ መተባበር።

### ማውጫ


I. ኃላፊነት እና ዓላማ
II. የቃላት መፍቻ
III. የሠራተኞች ምግባር መመዘኛዎች
IV. ትግበራ እና ክትትል
V. ቅሬታዎችን እና ስጋቶችን ሪፖርት ማድረግ
VI. መበቀል ያለመኖር

VII. ምርመራዎች

## I. ኃላፊነት እና ዓላማ

የቻይ ሥራ ሕፃናት እና ተጋላጭ ሕዝቦችን ጨምሮ ከተለያዩ የተጠቃሚዎች ስብስብ እና ሌሎች ጋር ሰራተኞቹን እንዲገናኙ ያደርጋል። በተጨማሪም በተለይም ሀብትን እና የንብረት ምደባን በሚቆጣጠሩበት ጊዜ ስራው ብዙ ሰራተኞችን በዕምነት እና በአንፃራዊ ስልጣን የሀላፊነት ደረጃዎች ላይ ያስቀምጣል።

የዚህ ፖሊሲ አላማ ለተጠቃሚዎች እና ለሕብረተሰቡ አባላት ደህንነቱ የተጠበቀ አካባቢን መፍጠር እና ልጆች እና ደካማ አዋቂዎችን ከቻይ ጋር በመገናኘታቸው ምክንያት ከሚከሰቱ ጉዳቶች መጠበቅ ነው። በተጨማሪም የወሲብ ብዝበዛ፣ በደል እና ትንኮሳ ክስተቶችን ለመፍታት የአሰራር ዘዴዎችን ማዘጋጀት እና ሰራተኞች በሁሉም የቻይ የሥራ አካባቢዎች ስላሉባቸው ሕጻናትን እና ደካማ አዋቂዎችን የመጠበቅ የውል እና የሞራል ኃላፊነቶችን ማሳወቅ ነው።

ይህ ፖሊሲ የቻይ ዓለም አቀፍ የአሰራር እና ሥነ-ምግባር ደንብ ቅጥያ ሲሆን በቻይ የበላይ አመራሮች ቡድን እና የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ተቀባይነት አግኝቷል። የቻይ ከፍተኛ የሰው ሀብት አስተዳደር ዳይሬክተር፣ ከቻይ ዋና ኦፕሬሽን ኦፊሰር ክትትል ስር ሆኖ የዚህን ፖሊሲ አፈፃፀም እና ክትትል ኃላፊነት ይዞ፣ የወሲብ ብዝበዛ፣ በደል እና ትንኮሳን ለመከላከል እንደከፍተኛው የሰው ሐብት አስተዳደር ዳይሬክተር ሆኖ ይሰራል።

## II. የቃላት መፍቻ

**ክስ፡** በቻይ ዓለም አቀፍ የአሰራር እና የሥነ-ምግባር ደንብ ውስጥ ሊፈፀሙ የሚችሉ ጥሰቶችን በተመለከተ በአንድ የሰራተኛ አባል የቀረበ መደበኛ ቅሬታ።

**ተጠቃሚ**: ከቻይ እንቅስቃሴዎች ድጋፍ የሚያገኝ፣ እናም በዚህ ምክንያት በተወሰነ መልኩ በቻይ ላይ ጥገኛ ወይም የሚተማመን ከቻይ የሰራተኛ አባል የተለየ አንድ ግለሰብ።

**ልጅ**፡ ወደ ጉርምስና የሚደርስበት የአገር ውስጥ ትርጉም ምንም ይሁን ምን ዕድሜው ከ18 ዓመት በታች የሆነ ማንኛውም ግለሰብ።

**ቅሬታ አቅራቢ፡** የወሲብ ብዝበዛ፣ በደል እና ትንኮሳ ተጠቂ የተባለው ሰው ወይም ጥፋቱን ያወቀና የጠቆመ/ክሱን ያስገባውን ሌላ ሰው ጨምሮ፣ ቅሬታውን ያቀረበው ሰው።

**ማስረጃ፡** በምርመራው ጊዜ የተሰበሰበ ክሱን የሚደግፍ ወይም የሚቃረን ማስረጃ።

**ማዕከላዊ ተጠሪ፡** የወሲባዊ ብዝበዛ፣ በደል እና ትንኮሳ ጉዳይ አቤቱታዎችን መቀበልን ጨምሮ ከወሲብ ብዝበዛ፣ በደል እና ትንኮሳ የመከላከል ፖሊሲ ጋር በተያያዘ ልዩ ኃላፊነቶችን እንዲወስድ በቻይ የተሰየመ አንድ ሰው።

**ዓለም አቀፍ የአሰራር እና የሥነ-ምግባር ደንብ፡** ሁሉም የቻይ ሰራተኞች የመከተል ግዴታ የተጣለባቸው የባህሪ መለኪያዎች ስብስብ።

**መርማሪ፡** አንድ የተለየ አቤቱታን ለመመርመር በቻይ ከፍተኛ ማዕከላዊ ተጠሪ ወይም ተወካይ የተመደበ ሰው። መርማሪው የሰለጠነ የቻይ ሰራተኛ አባል ወይም የውጭ መርማሪ ሊሆን ይችላል።

**አጋር፡** የቻይን ፕሮግራም ለመደገፍ ወሳኝ ሚና የሚጫወት ኤጀንሲ ወይም ድርጅት፣ ወሳኝ የማስተባበር ሚናን የሚተገብር ወይም በቻይ ስም እንቅስቃሴዎችን የሚያካሂድ።

**የወሲብ በደል**[2]**፡** በኃይል ወይም ተመጣጣኝ ባልሆነ ሁኔታ ወይም በማስገደድ፣ ወሲባዊ ባህርይ ያለው ማስፈራራት ወይም አካላዊ ጣልቃ ገብነት።

**የወሲብ ብዝበዛ**[3]: በገንዘብ፣ በማኅበራዊ ወይንም በፖለቲካዊ ጉዳዮች ሌሎችን በወሲብ በመበዝበዝ መበልጸግን ጨምሮ፣ በዚህ ብቻ ባይወሰንም፣ ማንኛውም የተጋላጭነትን ሁኔታ፣ የኃይል ልዩነትን ወይም ዕምነትን ለወሲባዊ ብዝበዛ መጠቀም ወይም ለመጠቀም መሞከር።

**ወሲባዊ ትንኮሳ**[4]: ማንኛውም ያልተፈለገ ወሲባዊ እንቅስቃሴ፣ ወሲባዊ ውለታን መጠየቅ፣ ወሲባዊ ባህሪ ያላቸው የቃል ወይም አካላዊ ምግባር ወይም ሌላ ዓይነት ወሲባዊ ምልክት፣ ለምሳሌ፣ እንደነዚህ ያሉ ተግባሮች በሥራ ላይ ጣልቃ ሲገቡ፣ ለሥራ እንደ ቅድመ ሁኔታ ሲቀመጡ፣ ወይም አስፈሪ፣ ጥላቻን የተላበሰ ወይም ጎጂ ሁኔታን ሲፈጥር። ወሲባዊ ትንኮሳ በአካል ወይም በስልክ በኢሜል፣ ወይም በማህበራዊ ሚዲያ የሚደረገውን ጨምሮ፣ በዚህ ብቻ ሳይወሰን፣ በርቀት ሊካሄድ ይችላል። በተለምዶ የባህሪ ቅጥን የሚይዝ ቢሆንም የአንድ ነጠላ ክስተት ቅርፅን ሊወስድም ይችላል። ወሲባዊ ትንኮሳ ተቃራኒ ጾታ ወይም ተመሳሳይ ጾታ ባላቸው ሰዎች መካከል ሊከሰት ይችላል። ሁሉም ፆታዎች አጥቂዎች ወይም ተጠቂዎች ሊሆኑ ይችላሉ።

**ወሲባዊ ያልተገቡ ባህሪያት፡** ለፖሊሲው አላማ ሲባል፣ ከላይ እንደተተረጎመው የወሲብ ብዝበዛ፣ በደል ወይም ትንኮሳ ድርጊቶችን ይመለከታል።

**ሰራተኛ /የሠራተኛ አባል፡**ቻይን የሚወክል ወይም በሙሉ ጊዜ ወይም በከፊል ጊዜ የሚሰራ ወይም የሚሳተፍ ሰው፣ ለሥራው/ዋ ወይም በውክልናው/ዋ የገንዘብ ክፍያ የሚያገኝ/የምታገኝ ሆነም አልሆነችም። ይህ የበጎ ፈቃደኞችን እና የሌሎች ጊዜያዊ ሰራተኞችንም ይጨምራል።

**አቤቱታው የቀረበበት ሰው** (SOC)**፡** ተጎጂው ላይ ወሲባዊ ብዝበዛ፣ በደል ወይም ትንኮሳ እንደፈጸመ ክስ የቀረበበት ወይም የተጠረጠረ ግለሰብ።

**ተጠቂ፡** ወሲባዊ ብዝበዛ፣ በደል ወይም ትንኮሳ የደረሰበት ሰው።

**ምስክር፡** ተጠቂውን፣ ቅሬታ ያስገባውን ሰው ጨምሮ፣ የአጋር ኤጀንሲ የስራ አባል፣ አቤቱታው የቀረበበት ሰው ወይንም ሌላ ሠራተኛ ለምርመራው አስፈላጊ ሊሆኑ የሚችሉ ማናቸውም መረጃዎች ያለው ማንኛውም ሰው።

## III. የሠራተኞች ምግባር መመዘኛዎች

ወሲባዊ ብዝበዛ፣ ወሲባዊ በደል እና ወሲባዊ ትንኮሳ ከባድ ያልተገባ ተግባርን የያዙ ሲሆን፣ *ማንኛውም እነዚህን መስፈርቶች መጣስ ወዲያውኑ ከየቅጥር ማቋረጥን ጨምሮ የዲሲፕሊን እርምጃ መሰረት ሊሆን ይችላል።* የወሲብ ብዝበዛ፣ የወሲብ በደል ወይም ወሲባዊ ትንኮሳ የሚፈጽም ማንኛውም የቻይ የስራ ባልደረባበተጨማሪም[1] በተገቢ ሕጎች የወንጀል ክስ ወይም ሌላ የሕግ እርምጃ ሊወሰድበት ይችላል።

1. የቻይ ሠራተኞች በወሲብ ብዝበዛ ተግባራት ውስጥ ወይም ከሌሎች ወሲባዊ በዝባዥ ተግባራት ሆን ብለው ጥቅም ማግኘት የለባቸውም። ለምሳሌ፣ አንድ የቻይ ሰራተኛ የእሱን/የሷን ኃላፊነት ወይም ሥልጣን በጥቅማጥቅሞች ምትክ ወሲባዊ ውለታን ለማግኘት የሚጠቀም ከሆነ ይህ የወሲብ ብዝበዛ ነው።

2. የቻይ ሠራተኞች በወሲብ በደል ተግባራት ውስጥ ወይም ከሌሎች ወሲባዊ በደል ተግባራት ሆን ብለው ጥቅም ማግኘት የለባቸውም። ለምሳሌ፣ አንድ የቻይ ሰራተኛ በወሲብ ድርጊት ለመሳተፍ ኃይልን ወይም ማስገደድን የሚጠቀም ከሆነ ይህ ወሲባዊ በደል ነው። እንደዚህ ዓይነቶቹ ተግባራት በዚህ ባይወሰኑም፣ ከመሳም ወይም በእጅ ከመንካት እስከ ከባድ የወሲብ ጥቃቶች እስከመፈጸም የሚደርሱ በደሎችን ይጨምራሉ።

3. የቻይ ሠራተኞች በወሲባዊ ትንኮሳ ተግባራት ውስጥ መሳተፍ የለባቸውም። ለምሳሌ፣ አንድ የቻይ ሰራተኛ ያልተፈለገ የቃል ወይም አካላዊ ድርጊትን፣ ወሲባዊ ወይም ወሲባዊ ይዘት ያላቸው ቀልዶችን ወይም ስለ ወሲባዊ ባህሪ እና/ወይም ስለአንድ ሰው የወሲብ ህይወት በጽሁፍ ወይም አሉባልታ ወሬ ሲጠቅስ፣ ይህ ወሲባዊ ትንኮሳ ነው።

4. የአካባቢው የሚፈቀድ ዕድሜ ምንም ይሁን ምን (ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች ከሆኑ) ልጆች ጋር ወሲባዊ ተግባር የተከለከለ ነው። የልጅን እድሜ አሳስቶ ማሰብ መከላከያ አይሆንም።

5. በወሲባዊ ተግባር ምትክ ገንዘብን፣ ሥራን፣ ዕቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን መስጠት ወይም የሌላ ሰውን ወሲባዊ ተግባር እንደ አንድ የልውውጥ ክፍል አድርጎ ማቅረብ ወይም ማቀናጀት ከሥራ ሰዓታት ውጪ ያለውን ጊዜ ጨምሮበጥብቅ የተከለከለ ነው። ይህም የወሲብ እንቅስቃሴን ለማስገደድ ጥቅም ላይ ከዋለ ለተጠቃሚዎች ድጋፍ መስጠት ወይም ማቅረብን ያጠቃልላል።

6. ቻይ ተጠቃሚዎች ከሚቀበሉት እርዳታ ጋር በቀጥታ በተያያዘ በቻይ ሠራተኞች እና ተጠቃሚዎች መካከል,፣ ያልተመጣጠነ የኃይል ሚዛን የቻይ ን ሥራን ተከባሪነት እና ተፅዕኖ ሊሸረሽር በሚችልበት ሁኔታ የሚደረግን ማንኛውንም ወሲባዊ ግንኙነትን ፈጽሞ አያበረታታም። አንድ የሠራተኛ አባል ስለተወሰነ ግንኙነት ተገቢነት ከማዕከላዊ ተጠሪ (ፎካል ፖይንት) ምክር መጠየቅ ይችላል። (ጥርጣሬን ለማስቀረት ሲባል፣ ይህ አንቀጽ ቀጥታ የግል እርዳታ ከሚደረግላቸው በስተቀር ከቻይ እንቅስቃሴዎች እርዳታ ለሚያገኙ ድርጅቶች ወይም

[1]

የመንግስት ኤጀንሲዎች የሚሰሩ ግለሰቦች ላይ አይተገበርም። የቻይ ዓለም አቀፍ የአሰራር እና የሥነ-ምግባር ደንብ በቻይ ሠራተኞች እና በእንደዚህ ዓይነቶቹ ግለሰቦች መካከል ያለውን ስነ-ምግባር ያገዛል።)

7. የቻይ አባል ሰራተኛ በቻይ ወይም በሌላ ድርጅት ውስጥ በሌላ ሰራተኛ የወሲብ ብዝበዛ፣ በደል ወይም ትንኮሳ በመሳሰሉ ጉዳዮች ላይ ስጋቶችች ወይም ጥርጣሬዎች ካጋጠሙት፣ ከዚህ በታች ከቀረቡት የአቤቱታ አቀራረብ ዝርዝሮች ውስጥ በአንዱ ወይም *ደንቡን ማስከበር እና ሪፖርት የማድረግ ስጋቶች* በሚለው የቻይ ዓለም አቀፍ የአሰራር እና የሥነ-ምግባር ደንብ ክፍል ስር ሪፖርት ማድረግ አለባቸው።

8. የቻይ ሰራተኞች የወሲብ ብዝበዛ፣ በደል እና ትንኮሳን የሚከለክል አካባቢን የመፍጠር እና የመጠበቅ ግዴታ አለባቸው። በማናቸውም ደረጃ ያሉ አስተዳዳሪዎች ይህንን አካባቢ የሚጠብቁ እና ለቀረቡ ማናቸውም ስጋቶች በአስቸኳይ ምላሽ መስጠት እና እርምጃዎችን የሚደግፉ ስርዓቶችን ማጎልበት እና ማጠናከር አለባቸው። በየደረጃው ያሉ አስተዳዳሪዎች ከእነርሱ ጋር የተነሱ አሳሳቢ ጉዳዮች ላይ ሪፖርት የማድረግ ስርዓቶችን መከተል አለባቸው።

የቻይ ሰራተኞች ከሌላ የቻይ ሰራተኞች ጋር የሚያደርጓቸውን ግንኙነቶች እና በቻይ ሰራተኞች እና ከቻይ ጋር አብረው የሚሰሩ አጋር ድርጅቶች ሰራተኞች እና የመንግስት ኤጀንሲዎች ጋር የሚገናኙ ጉዳዮችን በተመለከተ የቻይን ዓለም አቀፍ የምግባር የአሰራር እና የሥነ-ምግባር ደንብን (CHAI’s Global Code of Conduct and Ethics) ይመልከቱ።

## IV. ትግበራ እና ክትትል

ሁሉም የጥፋተኝነት ወይም ተገቢ ያልሆኑ ባህሪዎች ክሶች በቻይ ፖሊሲዎች እና ሂደቶች መሰረት በአግባቡ ይመረመራሉ። የወሲብ ብዝበዛን፣ በደልን እና ትንኮሳዎችን ለመከላከል እና ችግሮች ሲከሰቱ ተጠቂዎችን ለመጠበቅ ቻይ የተቻለውን ሁሉ ያደርጋል። ይህንን ቁርጠኝነት ለማሟላት፣ቻይ የሚከተሉትን እርምጃዎች ወስዷል፡

- ውጤታማነትን ለመከታተል እና መሻሻልን ሪፖርት ለማድረግ የወሲብ ብዝበዛን፣ በደልን እና ትንኮሳን ለመከላከል እና ምላሽ ለመስጠት የሚደረጉ ጥረቶችን ለመቆጣጠር የወሲብዝበዛን፣ በደልና ትንኮሳን የመከላከል (PSEAH) ፖሊሲዎች እና ፕሮቶኮሎችና ጥረቶችን ለዋና ኦፐሬቲንግ ኦፊሰር መስጠት።
- ለ PSEAH-ነክ ተግባራት እና ለማዕከላዊ ተጠሪ፣ ለሌሎች ማዕከላዊ ተጠሪዎች መርማሪዎችሃላፊነት ለመስጠት፣ ምርመራዎችን ለማስተዳደር፣ እና እንዳግባብነቱ ለዋና ኦፐሬቲንግ ኦፊሰር፣ ለከፍተኛ አመራሮች ቡድን (Senior Leadership Team) እና ለቦርዱ እንደአግባብነቱ ሪፖርት ለማድረግ የቻይ ከፍተኛ የሰው ሀብት አስተዳደር ዳይሬክተርን መሰየም።
- ተፈፃሚነት ያላቸውን ሕጎች በመከተል እና የቻይ አቅም በሚፈቅደው መጠን የወሲብ ብዝበዛ፣ በደል እና የትንኮሳ ወንጀለኞችን በቻይ ከመቀጠር ወይም መልሰው ከመቀጠር መከላከል። ይህም የኋላ ታሪክን እና የወንጀል ሪኮርዶችን ማጣራትን ሊያካትት ይችላል።
- የቻይ ሰራተኞችን በማሳተፍ የወሲብ ብዝበዛ፣ በደል እና ትንኮሳ ክሶችን በወቅቱ እና ሙያዊ አካሄድን በተከተለ ሁኔታ መመርመር እና የቻይ አቅም በሚፈቅደው መሰረት ሕጋዊ ሂደትን ማረጋገጥ። መርማሪዎች ለቅሬታ አቅራቢዎች፣ ተጠቂዎች እና አቤቱታ የቀረበባቸውን መብት እና ክብር በጠበቀ መልኩ ያለማዳላት ስራቸውን ያከናውናሉ። ይህም ቅሬታ አቅራቢዎችን እና ምስክሮች ተገቢውን የቃለ መጠይቅ አሰራሮችን መጠቀም እና በተለይም ከልጆች ጋር የሙያ መርማሪዎችን ተሳትፎ ወይም ተገቢውን የምርመራ

ባለሙያዎችን ማሳተፍን ያካትታል።ቻይ በምርመራዎቹ ግኝቶች ላይ እርምጃ ይወስዳል። የተገኙ ትምህርቶች እንደአግባብነታቸው ፖሊሲ እና ልምዶችን ለማሻሻል ጥቅም ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል።

- ለሁሉም የቻይ ሰራተኞች ከወሲብ ብዝበዛ፣ በደልና ትንኮሳ መከላከል ፖሊሲ (PSEAH) ጋር በሚዛመዱ ርእሰ-ጉዳዮች ላይ ተከታታይ ስልጠና መስጠት።
- የ ወሲብ ብዝበዛ፣ በደልና ትንኮሳ መከላከል ፖሊሲን (PSEAH) በአጋርነት፣ በንዑስ ድጋፍ ወይም በንዑስ-ተቀባይ ስምምነቶች ውስጥ ማካተት እና ይህን ፖሊሲ ጥሷል ተብሎ የሚታመንንማንኛውንም ድርጊት ወዲያውኑ ለቻይ ማሳወቅ እንዲኖርባቸው ማድረግ።

**የቻይ የእገዛ መስመሮች**
chai@integritycounts.ca
+1-866-921-6714 (ነፃ ጥሪ አሜሪካ)
+ 1-604-922-5953 (ኢንተርናሽናል)
www.integritycounts.ca

- ይህን መመሪያ በየጊዜው መከለስ እና ማዘመን።
- በወሲብ ብዝበዛ፣ በደል እና ትንኮሳ የተጎዱ እና ሌሎች ተጠቂዎች እንደአስፈላጊነቱ የአስቸኳይ እገዛ እና የስነ-ልቦና ድጋፍ ለማድረግ የሚያስችሉ ኃብቶች መኖራቸውን ማረጋገጥ።

## V. ቅሬታዎችን እና ስጋቶችን ማመልከት

የተከሰቱ ወይም ሊከሰቱ የሚችሉ ያልተገቡ የወሲብ ባህሪያት ወይም የዚህን ፖሊሲ መጣስ በተመለከተ ሁሉም ስጋቶች ወዲያውኑ ሪፖርት መደረግ አለባቸው።ቻይ ለማንኛውም ወሲባዊ ብዝበዛ፣ በደል ወይም ትንኮሳ ቅሬታዎች ወይም ጥርጣሬዎች ምንም እንኳ ይህ በወሬ/አሉባልታ ደረጃ ቢሆንም ምላሽ ይሰጣል። አንድ ሪፖርት ለማቅረብ አንድ ጉዳይን የሚደግፍ ማረጋገጫ መያዝ አስፈላጊ አይሆንም። አንድ ግለሰብ የፖሊሲውን መጣስ ሊያመለክት የሚችል አንድ ነገር ካየ ወይም ከሰማ ይህ ቅሬታ ለማስገባት በቂ ምክንያት ነው።

ቅሬታ አቅራቢዎች ሪፖርት በማድረግ ምንም ጉዳት እንደማይደርስባቸው፣ እንደሚሰሙ እና እርምጃ እንደሚወሰድ ማሰብ አለባቸው።ቻይ ሁሉም ሰራተኞች እና ተጠቃሚዎች ወደፊት ወጥተው በተቻለ መጠን በአስቸኳይ ማናቸውንም ስበመደበኛ ሁኔታ ያሏቸውን ስጋቶች እንዲያነሱ ለማበረታታት እና ለማጋለጥ ቁርጠኛ ነው። ሰራተኞች እና ተጠቃሚዎች የወሲብ ጥቃት፣ በደል እና ወሲባዊ ትንኮሳን፣ ማንኛውም ታሪካዊ ወይም ወቅታዊ ክሶችን ጨምሮ ሪፖርት ማድረግ በራስ መተማመን እና ምቾት ሊሰማቸው ይገባል።

ስለዚህቻይ ሁሉንም ስጋቶች በቁም ነገር እና በሚስጥራዊነት ይይዛቸዋል። ሰራተኞች በአካል ለመቅረብ ካልፈለጉ ስማቸውን ሳይገልጹ ሪፖርት ማድረግ ይችላሉ።

ቅሬታዎች እና ስጋቶች ከሚከተሉት መንገዶች ውስጥ በአንዱ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ሊቀርቡ ይችላሉ።

- **የቻይ ሰራተኞች ከራሳቸው ስራ አስኪያጅ ጋር መገናኘት፣**
- **የቻይን ከፍተኛ ማዕከላዊ ተጠሪን ወይም ሌላ ማዕከላዊ ተጠሪ ተብሎ የተሰየመን ሰው መገናኘት፣**
- **የቻይ እገዛ መስመርን መገናኘት።** የእገዛ መስመሩ የግለሰቦች የስነ-ምግባር ጉድለቶችን (በስም-አልባ

ወይም በስም) ሪፖርት እንዲያደርጉ የሚያስችሉ የሦስተኛ ወገን “የአሳባቂ” አገልግሎት ነው። ስም አልባ ሪፖርቶች ግለሰቦች ማንነታቸውን ገልጸው በጠቆሟቸው ሪፖርቶች ልክ ክብደት የሚሰጣቸው ይሆናል።

እያንዳንዱ የ**ቻይ** ሰራተኛ  በቻይ ሰራተኞች ወይም አጋር ድርጅቶች የሚፈጸም ወሲባዊ ብዝበዛን፣ በደልን ወይም ትንኮሳ የሚጠረጠሩ ጉዳዮችን ሪፖርት የማድረግ ሃላፊነት አለበት።

ስጋቶችን አሳስቶ ሆን ብሎ ሀሰተኛ መረጃዎችን  የሚጠቁም ማንኛውም ሰው ተፈጻሚ በሚሆነው ሕግ መሰረት የቅጣት እርምጃ ይወሰድበታል።

## VI. መበቀል ያለመኖር

ቻይ በዚህ ፖሊሲ፣ ዓለም አቀፍ የአሰራር እና የሥነ-ምግባር ደንብ መሰረት አቤቱታ ወይም ክርክር የሚያቀርቡ ሰራተኞችን ለመበቀል  ማንኛውም ዓይነት የትንኮሳ፣ የበቀል ወንጀለኛ ወይም አስከፊ የቅጥር ስራን አይታገስም። የተሳሳቱ ቢሆንም እንኳን ስጋቶች በእውነተኛ እምነት ሊነሱ ይችላሉ። ማንኛውም የቻይ የስራ ባልደረባ  ጉዳዩ በጥሩ ሁኔታ ያሳሰበውን ግለሰብ የሚበድል፣ የሚበቀል፣ ጥቃቶች የሚያደርስ፣  በተገቢው ሕግ መሰረት የቅጥር ውልን ማቋረጥ ጨምሮ   የቅጣት እርምጃ ይወሰድበታል።

## VII. ምርመራዎች

ሁሉንም ቅሬታ አቅራቢዎች፣ ሪፖርት አድራጊዎች እና የቅሬታ አቅራቢዎችን  ግላዊነት ለመጠበቅ ማንኛውም ጥረት ሁሉ ይደረጋል።ቻይ የተሟላ ምስጢራዊነትን ለመጠበቅ ዋስትና ሊሰጥ ስለማይችል ቅሬታዎች እና ምርመራዎች መረጃ ማወቅ ለሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች ብቻ የተገደቡ ናቸው። አቤቱታው የቀረበበት ግለሰብ የቻይ መሪ፣ ማዕከላዊ ተጠሪ ወይም የዓለም አቀፍ የሰው ሐብት ሠራተኞች አባል ከሆነ ቅሬታውን የሚቀበለው የትኩረት ማዕቀፍ የጥቅም ግጭት ሊፈጥሩ በሚችሉ ግለሰቦች ጉዳይ ላይ ላለመሳተፍ ቅደም ተከተሎችን ይከተላል።

ምርመራ በሚደረግበት ጊዜ እና ከምርመራው በኋላ፣ ሪፖርቱን ወይም ቅሬታውን የሚያውቅ ማንኛውም ሰው የጉዳዩን ሚስጥራዊነት እና አቤቱታ የቀረበበትን ሰው፣ የሪፖርት አድራጊው፣ የተጎጂውን እና ማንኛውንም የምስክሮች ማንነት እና ግላዊነት መጠበቅ ይኖርበታል። ከምርመራ ጋር የማይተባበሩ ወይም የምስጢራዊነት ጥሰትን የሚፈጽሙ ግለሰቦች በወቅቱ ተፈጻሚነት ባለው ሕግ እስከሚፈቅደው ድረስ የቅጣት እርምጃ ይወሰድባቸዋል።

የቻይ ማዕከላዊ ተጠሪዎች እና መርማሪዎች ቅሬታ አቅራቢውን፣ ተጎጂውን፣ ተጠርጣሪውን፣ ሪፖርት አድራጊውን እና ሌሎች ምስክሮችን ከቂም በቀል ለመጠበቅ እና በምርመራ ሂደቱ ውስጥ ደህንነታቸውን ለመጠበቅ አስፈላጊውን ተግባር ሁሉ  መውሰድ አለባቸው።